በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
እንጅባራ ዩኒቨርሲቲ
የፕሬዝዳንት ጽ/ቤት

እንጅባራ ዩኒቨርሲቲ
INJIBARA

The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Science and Higher Education
...ra University
...lent Office

ቁጥር 636/1-6
Ref. No.
ቀን 09/12/11
Date

- ለማህበራዊና ስብአዊ ሳይንስ ኮሌጅ
- ለግብርና፣ ምግብና የአየር ንብረት ሳይንስ ኮሌጅ
- ለተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ ኮሌጅ
- ለቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ
- ለእቅድ ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት
- ለሬጅስትራር ዳይሬክቶሬት
- ለቤተ-መጽሐፍትና ዶክመንቴሽን ዳይ/ሬት
- ለት/ት ጥራትና ማረጋገጫ ማጎልበቻና አዲቲንግ ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት
- ለምርምርና የማህ/አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለተከታታይና የርቀት ት/ት ማስ/ዳይሬክቶሬት
- ለሰው ሀብት ሥራ አመራርና ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለህዝብና የውጭ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት
- ለህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለተማሪዎች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት

እንጅባራ ዩኒቨርሲቲ፣

ጉዳዩ፡- የመካከለኛና መሠረታዊ አመራር ምርጫና አሰያየምን ለመደንገግ የወጣውን መመሪያን ስለመላክ

ዩኒቨርሲቲው የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 መሠረት በማድረግ በየደረጃው ያለው የአካዳሚክ ማህበረሰብና ኃላፊዎች የአመራር እና አስተዳደር ቦታዎችን ለማስያዝ የሚያስፈልጉ ብቃት፣ ክህሎት እና ልምድ ያላቸው ተወዳዳሪና ብቁ የሆኑ ግለሰቦችን የታወቁ ደረጃዎች እና መመዘኛዎችን በመከተል በኃላፊነት መመደብ እንዲቻል በባለቤትነት የሚፈጽሙበትን የአሠራር ሥርዓት እንዲኖር ለማድረግ የመካከለኛና መሠረታዊ አመራር ምርጫና አሰያየምን በተመለከተ የአፈጻጸም መመሪያ በማውጣት የዩኒቨርሲቲው ሴኔት በቀን 07/12/2011 ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ተወያይቶ አጽድቋል።

ስለዚህ ይህንን መመሪያ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን 9 ገጽ እየላክን መመሪያው ሴኔቱ ካፀደቀበት ዕለት ጀምሮ ተግባራዊ እንዲሆን እናሳስባለሁ።

"ከሠላምታ ጋር"

ብርሃኑ በላይ አቡኔ (ፒ/ር)
ፕሬዝዳንት

ግልባጭ//-
- ለፕሬዝዳንት ጽ/ቤት
- ለአካዳሚክና ምርምር ም/ፕሬዝዳንት
- ለአስተዳደር እና ልማት ም/ፕሬዝዳንት

እንጅባራ ዩኒቨርሲቲ፣


☎ - 0582272111
Fax: 0582270383
40
E-mail- www.inu.edu.et

INJIBARA
UNIVERSITY

# በእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ
# የመካከለኛና መሠረታዊ አመራር
# ምርጫና አስያየምን ለመደንገግ
# የወጣ መመሪያ

ነሐሴ 2011 ዓ.ም

እንጅባራ ዩኒቨርሲቲ

## መግቢያ

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አስተዳደር፡ ጥራት ያለው ትምህርት፡ ምርምርና አዲስ የፈጠራ ሥራ ለማቅረብ፡ የማህበረሰብ አገልግሎቶችን በማስፋፋትና የማህበረሰብ ፍላጎቶችን ለማሟላት ወሳኝ ሚና እንዳላቸው የታመነበት በመሆኑ፡

የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር የሠራተኞችን ተነሳሽነት ለመጨመር ብሎም ተቋማዊ ብቃትን ለማሳደግ መልካም አስተዳደር ማስፈን እንዲቻል የአመራር እና የአስተዳደር ቦታዎች ሹመት ችሎታን ባማከለ ውድድር ላይ ተመስርቶ እንዲሆን የሚፈቅድ አሳታፊ እና ግልጽ የሆነ አሰራር አስፈላጊነትን የሚያምን በመሆኑና እንጅባራ ዩኒቨርስቲም ይህን በቁርጠኝነት ለመተግበር በመወሰኑ፡

በእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ በየደረጃው የሚገኙ መሪዎች በችሎታ ላይ የተመሠረተ ሹመትና ምደባ ግልጽ እና አሳታፊ ሥርዓትን የተከተለ እንዲሆን ለማድረግና በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ለአካዳሚክ የሥራ ቦታዎች ተመርጠው ለሚሾሙ/ለሚመደቡ፡ የእጩ መልማይና ምርጫ ኮሚቴዎች፡ በየደረጃው የሚገኙ አመራሮች ተመርጠው የሚሾሙባቸውን ዓላማዎች፡ ሥርዓቶችና መስፈርቶች ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ፡

በሙያቸው የሰለጠኑ፡ ብቃት፡ ችሎታ እና እምነት የሚጣልባቸውን ግለሰቦች ወደ አመራርነት እና የአስተዳደር ስራ መድረክ በማምጣት የዩኒቨርስቲውን የትምህርት ጥራትና ተገቢነት ለማሻሻል፡ ችግር ፈቺ ምርምሮችንና የማህበረሰብ አገልግሎት ተግባራትን ለማከናወን ይቻል ዘንድ በትምህርት ክፍሎች ወጥ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፡

በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 49(3) እና በእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ የሴኔት ሕግ /ሌጅስሌሽን/ አንቀጽ 9(4) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህ መመሪያ ወጥቷል፡፡

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "በእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ የመካከለኛና መሠረታዊ አመራር ምርጫ፣ ሹመት/ምደባ ለመደንገግ የወጣ መመሪያ ቁጥር …/2011" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጉም

በዚህ መመሪያ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡

1. "አዋጅ" ማለት የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 ነው፡፡
2. "ዩኒቨርሲቲ" ማለት እንጅባራ ዩኒቨርሲቲ ነው፡፡
3. "አካዳሚክ ማህበረሰብ" ማለት በእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ በመደበኛነት ወይም በጊዜያዊነት በመማር፡ ማስተማር፡ በምርምርና በማህበረሰብ አገልግሎት ተግባራት ወይም ሥራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ሰዎችን ያቀፈ ነው፡፡

4. "መካከለኛ አመራር" ማለት የኮሌጅ ዲኖችን፣ ም/ዲኖችን፣ ዳይሬክተሮችን፣ ም/ዳይሬክተሮችን እና በተመሳሳይ ወይም አቻ ማዕረግ የሚሾሙ ሌሎች ኃላፊዎችን ያካትታል፡፡
5. "መሠረታዊ አመራር" ማለት የትምህርት ክፍል ኃላፊዎችን፣ የኮሌጅ የትምህርት መርሀ-ግብር አስተባባሪዎች፣ አፊሰሮች እና በተመሳሳይ ወይም አቻ ማዕረግ የሚመደቡ ኃላፊዎችን ያካትታል፡፡
6. "ዳይሬክተር" ማለት የምልመላ እና የቅጥር ሥርዓት በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግ የማይገዛውን የዩኒቨርሲቲው በተለያዩ የሥራ ክፍሎች ኃላፊ ማለት ነው፡፡
7. "ዲን" ማለት በዩኒቨርሲቲው የሴኔት ሌጅስሌሽን የተጠቀሰው የኮሌጅ /የተቋም/ የት/ቤት ወይም የአካዳሚ ኃላፊ ማለት ነው፡፡
8. "አካዳሚክ ዩኒት" ማለት በአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 2/4 እና በዩኒቨርሲቲው የሴኔት ሌጅስሌሽን አንቀጽ 2(5) ስር የተዘረዘሩት ተቋማዊ ክፍሎች ናቸው፡፡
9. በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፁት ቃላቶች ለሴት ፆታም ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች በእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ማህበረሰብ ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## 4. ግብ እና ዓላማዎች

መመሪያው በእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ፡-

1) የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ባስቀመጠው የአመራር እና አስተዳደር ቦታዎችን ለማስያዝ የሚያስፈልጉ ብቃት፣ ክህሎት እና ልምድ ያላቸው ተወዳዳሪና ብቁ የሆኑ ግለሰቦችን መሾም/መመደብ እንዲቻል፣
2) የግለሰቦች ሹመት/ምደባ በሙያ፣ በብቃታቸውና በውድድር ላይ የተመሰረተ መሆኑን ለማረጋገጥ እንዲቻል፣
3) እጩዎችን ለመመልመል እና ለመገምገም ዩኒቨርሲቲው የሚከተለው ሂደት በግልጽ የሚታወቅ፣ የታወቁ ደረጃዎች እና መመዘኛዎችን የተከተለ ፍትሃዊ፣ ግልጽ፣ ዴሞክራሲያዊ እና ተዓማኒነት ያለው ሂደት መሆኑን ለማረጋገጥ እንዲቻል፣
4) የሹመትና ምደባ ስርዓቱ በእኩልነት ላይ የተመሰረተ፣ የጾታና የሙያ ስብጥርን ያለመ ሆኖ እንዲሰራ አቅጣጫ ለማሳየት የወጣ ነው፡፡

## 5. የዩኒቨርሲቲ መካከለኛና መሠረታዊ አመራሮች አመራረጥና አሰያየም

### 5.1. ለዲኖች ም/ዲኖች የት/ት ክፍል ኃላፊዎች እና ዳይሬክተሮች የእጩ መልማይና ምርጫ ኮሚቴዎችን ስለማቋቋም

(1) ዩኒቨርሲቲዎች መካከለኛና መሠረታዊ አመራሮችን መርጦ ለመመደብ የሚረዱ የዕጩ መልማይና ምርጫ ኮሚቴ ማቋቋም እንደሚችሉ በሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት

ኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ትምህርት ሚኒስቴር
እንጅባራ ዩኒቨርሲቲ
F.D.R.E Ministry of Education
Injibara University

ተቋማት የአመራርና አስተዳዳሪዎችን ምርጫ፣ ሹመት/ምደባ ለመደንገግ በወጣው መመሪያ ቁጥር 002/2011 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1(4) በተገለጸው መሠረት የእንጅባራ ዩኒቨርሲቲም በተለያዩ ትምህርት ክፍሎች ለዲኖች፣ ም/ዲኖች፣ ዳይሬክተሮች፣ የትምህርት ክፍል ኃላፊዎችና በእነዚህ ደረጃ ያሉ የኃላፊነት ቦታዎችን መርጦ ለመሾም የሚረዱ ዕጩ መልማይና ምርጫ ኮሚቴዎች የሚቋቋሙ ይሆናል፡፡

(2) ለዳይሬክተር ምርጫ አምስት አባላት ያሉት ከተለያዩ የስራ ክፍሎች በፕሬዝዳንቱና ጉዳዩ በሚመለከተው ም/ፕሬዝዳንት የሚመረጡ የእጩ መልማይና ምርጫ ኮሚቴ የሚቋቋም ይሆናል፡፡

(3) ለአካዳሚክ ዲን እና ም/ዲን ምርጫ አምስት አባላት ያሉት የዕጩ መልማይና ምርጫ ኮሚቴ የሚቋቋም ሲሆን የኮሚቴው ስብጥርም፡-

ሀ) በፕሬዝዳንት የሚመረጥ አንድ ተወካይ ........................................ሰብሳቢ

ለ) በሚመለከተው የአካዳሚክ ዩኒት ኮሚሽን አባላት ውስጥ የሚመረጥ አንድ ሰው ..............አባል

ሐ) በአካዳሚክ ዩኒቱ /ኮሌጁ/ መምህራን የሚመረጥ አንድ የመምህራን ተወካይ ..................አባል

መ) በአካዳሚክ ዩኒት /ኮሌጁ/ ተማሪዎች ህብረት የሚመረጥ አንድ የተማሪዎች ተወካይ.........አባል

ሠ) በአካ/ም/ም/ፕሬዝዳንቱ የሚመረጥ አንድ ተወካይ..........................................አባልና ፀሐፊ

(4) ለትምህርት ክፍል ኃላፊ ምርጫ አራት አባላት ያሉት የዕጩ መልማይና ምርጫ ኮሚቴ የሚቋቋም ሲሆን የኮሚቴው ስብጥርም፡-

ሀ) በሚመለከተው የአካዳሚክ ዩኒት ኮሚሽን አባላት ውስጥ የሚመረጥ አንድ መምህር...........ሰብሳቢ

ለ) በሚመለከተው የዲፓርትመንት ካውንስል አባላት መካከል የሚመረጥ አንድ መምህር........አባል

ሐ) ከትምህርት ክፍሉ የተማሪዎች ህብረት የሚመረጥ አንድ የተማሪዎች ተወካይ.............አባል

መ) ከትምህርት ክፍሉ መምህራን መካከል በዲን የሚመረጥ አንድ መምህር.................አባልና ፀሐፊ

(5) በዕጩ መልማይና ምርጫ ኮሚቴነት የሚመረጡ ሰዎች በተቋሙ ማህበረሰብ የተከበሩና የተሻለ የትምህርት ደረጃ ያላቸው፣ እንዲሁም ስለክፍት የሥራ ቦታው ባህሪና ተገቢው ሰው ጥሩ የማመዛዘን ችሎታ እና ግልጽ የሆነ ግንዛቤ ያለው ሊሆን ይገባል፡፡

(6) የዕጩ መልማይና ምርጫ ኮሚቴ አባል ውድድር ለሚካሄድበት የኃላፊነት ቦታ በዕጩነት ቀርቦ ለመወዳደር ሲፈልግ በሌላ ውድድሩ ላይ መሳተፍ በማይፈልግ ዕጩ መልማይ እንዲተካ ይደረጋል፡፡

(7) ዕጩ መልማይና ምርጫ ኮሚቴ የአገልግሎት የሥራ ዘመን ለሁለት ዓመት ይሆናል፡፡

## 5.2 የምልመላ እና ምርጫ ኮሚቴዎች ተግባርና ኃላፊነት

1) የምልመላ እና ምርጫ ኮሚቴው ስብሰባዎችን የሚያዘጋጅ ሲሆን የምልመላ፣ የማጣሪያ እና የምርጫ ሂደት የጊዜ ሰሌዳን ጨምሮ የኮሚቴውን የአሠራር ዘዴዎች ያዘጋጃል፡፡

ሀ) የኃላፊነት ቦታዎች ለአካዳሚክ ዩኒቱ ወይም እንደአስፈላጊነቱ ለዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ ማህበረሰብ በግልጽ እንዲታወቁ ማድረግ፣

ለ) ማስታወቂያ ለወጣባቸው የሥራ መደቦች ተወዳዳሪዎችን መለየት

ሐ) የአመልካቾችን መረጃ መዝግቦ መያዝ፣

መ) ማስታወቂያ ለወጣባቸው የሥራ መደቦች በተወዳዳሪዎች የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን፣ የትምህርት ማስረጃዎችን፣ የሥራ ልምዶች እና የምስክር ወረቀቶችን መቀበል፣

ሠ) በተቀመጠው አሠራር መሠረት ተወዳዳሪዎችን መገምገም፣ ማነጋገርና ለይቶ ማወጣት፣

ረ) እንደአስፈላጊነቱ የውይይትና የግምገማ ስብሰባዎችን ማዘጋጀትና ማመቻቸት፣

ሰ) ዕጩ ተወዳዳሪዎች በሚያቀርቡት ስትራቴጂክ እቅድ እና ቃለ መጠይቅ መሠረት በአካዳሚክ ዩኒት ኮሚሽን፣ በትምህርት ክፍል ካውንስል አባላት እና በመምህራን የሚሰጠውን ድምጽ መሰብሰብ፣

ሸ) የዕጩ ተወዳዳሪዎች ምዘና ውጤት መግለጫና ስም ዝርዝራቸውን ባገኙት ውጤት መሠረት ማዘጋጀት፣

ቀ) የምርጫ ሂደቱን መቆጣጠር፣

በ) ምርጫውን የሚመለከት አጠቃላይ መግለጫ ማቅረብ፣

## 5.3 <u>የአካዳሚክ ዩኒት ዲንና ም/ዲኖች ምርጫና አሰያየም</u>

(1) በአካዳሚክ ክፍሎች ያሉ ዲኖች ወይም ምክትል ዲኖች ተመርጠው የሚመደቡበት ሂደት ለሚመለከተው የአካዳሚክ ማህበረሰብ ግልጽ መሆን አለበት፡፡

(2) የምልመላና ምርጫ ኮሚቴ ዕጩዎችን ከለየ በኋላ ባስመዘገቡት ውጤት ቅደም ተከተል 3 ዕጩዎችን ለዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ያቀርባል፡፡ ፕሬዝዳንቱም ከአካዳሚክ ምርምር /ም/ፕሬዝዳንት ጋር በመነጋገር ከቀረቡለት ዕጩዎች ውስጥ አንዱን ዲን ወይም ምክትል ዲን አድርጎ ይሾማል፡፡

(3) የአካዳሚክ ዩኒቱና የዩኒቨርሲቲው ፍላጎቶችንና ስልታዊ አቅጣጫዎችን የሚያሟሉ ዕጩ ተወዳዳሪዎችን ለሹመት የሚያቀርቡ ይሆናል፡፡ የአካዳሚክ ዩኒት ዲን ወይም ም/ዲኖች ዕጩ ተወዳዳሪዎች ብቃትና ዝግጁነት የሚከተሉትን መመዘኛዎች ተግባራዊ በማድረግ የሚወሰን ይሆናል፡፡

### ሀ) የትምህርት ደረጃ (25 ከመቶ)፡-

ውጤት አሰጣጡም፡- የፕሮፌሰርነት ማዕረግ ያለው (25 ነጥብ)፣ የተባባሪ ፕሮፌሰርነት ማዕረግ ወይም የሦስተኛ (PhD) ዲግሪ ያለው (20 ነጥብ)፣ የረዳት ፕሮፌሰርነት ማዕረግ ያለው (15 ነጥብ) እና የሁለተኛ ዲግሪ ማዕረግ ላለው (10 ነጥብ) የሚሰጥ ይሆናል፡፡

### ለ) የሥራ ልምድ (25 ከመቶ)፡-

በከፍተኛ ትምህርት ወይም ከዚህ ውጪ ባለ አቻ የትምህርት፣ የምርምር ተቋምና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ተቋማት የተገኘ የአመራርነት የሥራ ልምድ ያለው፤

ውጤት አሰጣጡም ከመቶ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

I) በማስተማርና ምርመር ሥራ አስር ዓመትና ከዚያ በላይ አገልግሎት ላለው እጩ ተወዳዳሪ 15 ነጥብ ዋጋ ይኖረዋል፡፡ ከአስር ዓመት በታች አገልግሎት ያለው ከላይ በተሰጠው ከፍተኛ ነጥብ መሠረት ባገለገለው ዓመት ልክ እየተሰላ የሚሰጥ ይሆናል፡፡

II) የአመራርነት ወይም የኃላፊነት አገልግሎት /ልምድ/ የሚይዘው ከፍተኛ ውጤት 10 ነጥብ ሆኖ የነጥብ አያያዙም በመሠረታዊ አመራርነት ለሰራ ለአንድ ዓመት አገልግሎት 2 ነጥብ፣ በመካከለኛ አመራርነት ለሰራ ለአንድ ዓመት አገልግሎት 2.5፣ በከፍተኛ አመራርነት ለሰራ ለአንድ ዓመት 3 ነጥብ እየታሰበ የሚፈፀም ይሆናል፡፡

III) በኢንዱስትሪውና ዓለም አቀፍ ተቋማት ተሳትፎ የሚገኝ የሥራ ልምድ በአገልግሎት ዘመን ላይ የተመሰረተ ሆኖ በማስተማርና በምርምር አገልግሎት ከሚገኘው ልምድ ጋር እኩል ነው፡፡

**ሐ) ዋና ዋና ተግባራትን ለማስፈጸም የሚቀርብ ንድፈ ሀሳብ ዝግጅትና አቀራረብ (20 ከመቶ)፡**

ለመልማይና ምርጫ ኮሚቴው እና ለአካዳሚክ ዩኒቱ ኮሚሽን አባላት የሚቀርብ የስትራቴጂክ እቅድ ዝግጅት፣ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በሚከተሉት አቅጣጫዎች ላይ ተገምግመው ለእያንዳንዱ እጩ ውጤት የሚሰጣቸው ይሆናል፡፡

I. የዕጩ ተወዳዳሪው በብቃት ለመምራት ያለው አቅም አዲስ ሀሳቦችን ለማፍለቅና ለተማሪዎች ተግባራዊ በሆነ መንገድ ለማድረስ ያለው ትጋት፣ የትንተና እና ስትራቴጂካዊ ክህሎቶች፣ ስለ ከፍተኛ ትምህርት ያለው ጠንካራ ግንዛቤ (5 ነጥብ)፤

II. ተወዳዳሪው የሚያቀርበው ርዕይና ተልዕኮ ይዘትና የሚሰጠው ማብራሪያ፡- ስለሚከተለው የስራ አመራርና በቀጣይ ሊሰራቸው ስላሰባቸው  እቅዶች፣ ተቋሙን ዓለማቀፋዊና ተወዳዳሪ ለማድረግ ያለው ብቃት፣ ከመንግስትና በጎ አድራጊዎች ገቢ ለማስገኘትና ሀብት ለማፍራት ስላለው እቅድና ስለሚያደርገው ጥረት (5 ነጥብ)፤

III. ለትምህርት ልህቀትና ለአካዳሚክ ነፃነት መሻሻል ያለው ቁርጠኝነት (5 ነጥብ)፤

IV. ቃለ-መጠይቅና ገለፃ፡- የምርጫ ኮሚቴው እና የአካዳሚክ ዩኒቱ ካውንስል አባላት በሚያነሷቸው ጥያቄዎች ላይ በሚሰጥ ማብራርያ አመልካቹ ስላለው የማስረዳት ተነሳሽነትና ተግባቦት፣ ለተነሱ ጥያቄዎች የሚሰጠው ምላሽ (5 ነጥብ)፤

**መ) የለውጥ ሥራ አመራር፣ ውጤታማነትና መልካም ሥነ-ምግባር (15 ከመቶ)፡-**

የመልማይና ምርጫ ኮሚቴው እና የአካዳሚክ ዩኒቱ ኮሚሽን አባላት ለእያንዳንዱ ዕጩ ተወዳዳሪ በሚከተሉት አቅጣጫዎች ላይ ተገምግመው ውጤት የሚሰጣቸው ይሆናል፡፡

I. የአሠራር ለውጡን ለመቀበል ያለው ዝግጁነትና ተነሳሽነት (4 ነጥብ)፡- ያለውን ዕውቀት ተጠቅሞ ሥራውን በጥራትና በውጤታማነት የሚያከናውን፣ የሚያጋጥሙ የአፈጻጸም ችግሮችን ለመፍታት አማራጭ የመፍትሄ ሀሳብ የሚያቀርብ፤ በእቅዱ መሰረት ስራውን በብቃት የሚያከናውን እንዲሁም የስራ መረጃ የሚይዝና በወቅቱ ሪፖርት የሚያቀርብ፤

II. ሙያዊ ብቃትና ውጤታማነት (4 ነጥብ)፡- የሁለት ሴሚስተር የስራ አፈጻጸም ግምገማ አማካይ ውጤት፤

III. የአመራር ብቃትና ውጤታማነት (4 ነጥብ)፡- መልካም አስተዳደር ለማስፈን ያለው ብቃት፤ የተሰጠውን ኃላፊነት በብቃትና በወቅቱ የሚወጣ እና ለስራውና ለህብረተሰቡ ቀና አስተሳሰብ ያለው፤

IV. መልካም ስነ ምግባር ያለው (3 ነጥብ)፡- ከሥራው ጋር በተያያዘ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሙስና የማይፈጽም፣ የመንግስትን ሀብት ወይም መሳሪያ ወይም የሥራ ጊዜ ወይም መረጃ ለግል ጥቅሙ የማያውል፤

## ሠ) በአካዳሚክ ክፍሉ መምህራን የሚሰጥ ድምጽ (15 ከመቶ)፡-

የሚከተሉትንና ሌሎች የአካዳሚክ ዩኒቱ ተግባራትን አፈጻጸም ግምት ውስጥ በማስገባት መራጮች ለተወዳዳሪዎች ነጥብ ይሰጣሉ፡፡

I. የሀገር አቀፍ የትምህርት ፖሊሲዎችን የማስፈጸም ቁርጠኝነትና የአካዳሚክ አመራርነት (4 ነጥብ)፤

II. የምርምርና የማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎች ተሳትፎ እና የግል ተነሳሽነት፣ የተግባቦት ክህሎት፣ መልካም ስምና ሀቀኝነት (4 ነጥብ)፤

III. የስትራቴጂካዊ አስተዳደር እውቀት፣ ከውጭ ሀገርና ሀገር ውስጥ ካሉ ተቋማት ጋር ግንኙነት የመፍጠር ብቃት (4 ነጥብ)፤

IV. የትምህርት ክፍሎችን እና የዩኒቨርሲቲውን ዕቅድ የመፈጸምና የማስፈጸም ቁርጠኝነት (3 ነጥብ)፤

## 5.4 <u>የትምህርት ክፍል ኃላፊ ምርጫና አሰያየም</u>

(1) በአካዳሚክ ክፍሎች ያሉ የትምህርት ክፍል ኃላፊዎች ወይም በትምህርት ክፍል ኃላፊ ደረጃ ያሉ አቻ የኃላፊነት ቦታዎች ተመርጠው የሚመደቡበት ሂደት ለሚመለከተው የትምህርት ክፍል ማህበረሰብ ግልጽ መሆን አለበት፡፡

(2) የምልመላና ምርጫ ኮሚቴ ዕጩዎችን ከለየ በኋላ ባስመዘገቡት ውጤት ቅደም ተከተል 3 ዕጩዎችን ለአካዳሚክና ም/ም/ፕሬዝዳንት ያቀርባል፡፡ ም/ፕሬዝዳንቱም ከኮሌጅ ዲን በመነጋገር ከቀረቡት ዕጩዎች ውስጥ አንዱን የትምህርት ክፍል ኃላፊ አድርጎ ይሾማል፡፡

(3) የትምህርት ክፍሉና የዩኒቨርሲቲው ፍላጎቶችንና ስልታዊ አቅጣጫዎችን የሚያሟሉ ዕጩ ተወዳዳሪዎችን ለምደባ የሚያቀርቡ ይሆናል፡፡ የትምህርት ክፍል ኃላፊዎች ወይም በነዚህ ደረጃ ያሉ የስራ ክፍል ኃላፊ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ብቃትና ዝግጁነት የሚከተሉትን መመዘኛዎች ተግባራዊ በማድረግ የሚወሰን ይሆናል፡፡

## ሀ) የትምህረት ደረጃ (25 ከመቶ)፡-

ውጤት አሰጣጡም፡- ሙሉ ፕሮፌሰርነት ማዕረግ ያለው (25 ነጥብ)፣ የተባባሪ ፕሮፌሰርነት ማዕረግ ወይም የሶስተኛ (PhD) ዲግሪ ያለው (20 ነጥብ)፣ የረዳት ፕሮፌሰርነት ማዕረግ ያለው (15 ነጥብ) እና የሌክቸረርነት ማዕረግ ላለው (10 ነጥብ) የሚሰጥ ይሆናል፡፡

## ለ) የሥራ ልምድ (25 ከመቶ)፡-

በከፍተኛ ትምህርት ወይም ከዚህ ውጪ ባለ የትምህርት፣ የምርምር ተቋምና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ተቋማት የተገኘ የአመራርነት የሥራ ልምድ ያለው፤

ውጤት አሰጣጡም፡-

I) በማስተማርና ምርመር ሥራ ስምንት ዓመትና ከዚያ በላይ አገልግሎት ላለው እጩ ተወዳዳሪ 15 ነጥብ ዋጋ ይኖረዋል፡፡ ከስምንት ዓመት በታች አገልግሎት ያለው ከላይ በተሰጠው ከፍተኛ ነጥብ መሠረት ባገለገለው ዓመት ልክ እየተሰላ የሚሰጥ ይሆናል፡፡

II) የአመራርነት ወይም የኃላፊነት አገልግሎት /ልምድ/ የሚይዘው ከፍተኛ ውጤት 10 ነጥብ ሆኖ የነጥብ አያያዙም በመሠረታዊ አመራርነት ለሰራ ለአንድ ዓመት አገልግሎት 1.5 ነጥብ፣ በመካከለኛ አመራርነት ለሰራ ለአንድ ዓመት አገልግሎት 2፣ በከፍተኛ አመራርነት ለሰራ ለአንድ ዓመት 2.5 ነጥብ እየታሰበ የሚፈፀም ይሆናል፡፡

## ሐ) የለውጥ ሥራ አመራር፣ ውጤታማነትና መልካም ስነ-ምግባር (25 ከመቶ)፡-

የመልማይና ምርጫ ኮሚቴው እና የትምህርት ክፍሉ ካውንስል አባላት ለእያንዳንዱ ዕጩ ተወዳዳሪ በሚከተሉት አቅጣጫዎች ላይ ተገምግመው ውጤት የሚሰጣቸው ይሆናል፡፡

I) የዕጩ ተወዳዳሪው በብቃት ለመምራት ያለው አቅም አዲስ ሀሳቦችን ለማፍለቅና ለተማሪዎች ተግባራዊ በሆነ መንገድ ለማድረስ ያለው ትጋት፣ የትንተና እና ስትራቴጂካዊ ክህሎቶች፣ ስለ ከፍተኛ ትምህርት ያለው ጠንካራ ግንዛቤ (4 ነጥብ)፤

II) የአሠራር ለውጡን ለመቀበል ያለው ዝግጁነትና ተነሳሽነት (4 ነጥብ)፡- ያለውን ዕውቀት ተጠቅሞ ስራውን በጥራትና በውጤታማነት የሚያከናውን፣ የሚያጋጥሙ የአፈጻጸም ችግሮችን ለመፍታት አማራጭ የመፍትሄ ሀሳብ የሚያቀርብ፣ በእቅዱ መሰረት ስራውን በብቃት የሚያከናውን እንዲሁም የስራ መረጃ የሚይዝና በወቅቱ ሪፖርት የሚያቀርብ፤

III) ሙያዊ ብቃትና ውጤታማነት (4 ነጥብ)፡- የሁለት ሴሚስተር የስራ አፈጻጸም ግምገማ አማካይ ውጤት፤

IV) የአመራር ብቃትና ውጤታማነት (4 ነጥብ)፡- መልካም አስተዳደር ለማስፈን ያለው ብቃት፣ የተሰጠውን ኃላፊነት በብቃትና በወቅቱ የሚወጣ እና ለሥራውና ለህብረተሰቡ ቀና አስተሳሰብ ያለው፤

V) መልካም ሥነ-ምግባር ያለው (4 ነጥብ)፡- ከስራው ጋር በተያያዘ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሙስና የማይፈጽም፣ የመንግስትን ሀብት ወይም መሣሪያ ወይም የሥራ ጊዜ ወይም መረጃ ለግል ጥቅሙ የማያውል፤

VI) ቃለ-መጠይቅና ገለፃ (5 ነጥብ)፡- የኮሚቴው አባላት በሚያነሷቸው ጥያቄዎች ላይ በሚሰጥ ማብራሪያ አመልካቹ ስላለው የማስረዳት ተነሳሽነትና ተግባቦት፣ ለተነሱ ጥያቄዎች የሚሰጠው ምላሽ፤

F.D.R.E Ministry

**መ) በትምህርት ክፍሉ መምህራን የሚሰጥ ድምጽ (25 ከመቶ)፡-**

የሚከተሉትንና ሌሎች የአካዳሚክ ዩኒቱ ተግባራትን አፈጻጸም ግምት ውስጥ በማስገባት መራጮች ለተወዳዳሪዎች ነጥብ ይሰጣሉ፡፡

I) የአገር አቀፍ የትምህርት ፖሊሲዎችን የማስፈጸም ቁርጠኝነትና የአካዳሚክ አመራርነት (5 ነጥብ)፣

II) የምርምርና የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራዎች ተሳትፎ፣ ለትምህርት ልህቀትና ለአካዳሚክ ነፃነት መሻሻል ያለው ቁርጠኝነት (5 ነጥብ)፣

III) የግል ተነሳሽነት፣ የተግባቦት ክህሎት፣ መልካም ስምና ሀቀኝነት (5 ነጥብ)፡

IV) የስትራቴጂካዊ አስተዳደር እውቀትና ከሌሎች ተቋማት ጋር ግንኙነት የመፍጠር ብቃት (5 ነጥብ)፡

V) የትምህርት ክፍሉን፣ የአካዳሚክ ዩኒቱን እና የዩኒቨርሲቲውን እቅድ የመፈጸምና የማስፈጸም ቁርጠኝነት (5 ነጥብ)፣

## 5.6. የዳይሬክተሮች ምርጫና አሰያየም

(1) ከአካዳሚክ ዩኒቶች ውጭ በተለያዩ ክፍሎች ያሉ ዳይሬክተሮች ተመርጠው የሚሾሙበት ሂደት ለሚመለከተው የአካዳሚክ ማህበረሰብ ግልጽ መሆን አለበት፡፡

(2) የምልመላና ምርጫ ኮሚቴ ዕጩዎችን ከለየ በኋላ ባስመዘገቡት ውጤት ቅደም ተከተል 3 ዕጩዎችን ለዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ያቀርባል፡፡ ፕሬዝዳንቱም ከሚመለከተው ወይም አግባብ ባለው ም/ፕሬዝዳንት ጋር በመነጋገር ከቀረቡለት ዕጩዎች ውስጥ አንዱን ዳይሬክተር አድርጎ ይሾማል፡፡

(3) የዳይሬክቶሬት ጽ/ቤቱና የዩኒቨርሲቲው ፍላጎቶችንና ስልታዊ አቅጣጫዎችን የሚያሟሉ ዕጩ ተወዳዳሪዎችን ለሹመት የሚያቀርበ ይሆናል፡፡

(4) የዳይሬክተር ኃላፊነት ምርጫና አሰያየም የነጥብ አያያዝን በተመለከተ ከላይ በቁጥር 5.3 (ከሀ-መ) ሥር ለአካዳሚክ ዩኒት ዲንና ም/ዲን የተገለጹት መስፈርቶችና መመዘኛዎች የሚያገለግሉ ሆነው በዚሁ ተራ ቁጥር "ሐ" እና "መ" ሥር በተቀመጡ አቅጣጫዎች መሠረት በምርጫ ኮሚቴው እና በሴኔት አባላት ተገምግመው ውጤት የሚሰጣቸው ይሆናል፡፡

(5) የሚከተሉትንና ሌሎች የዳይሬክቶሬቱ ተግባራትን አፈጻጸም ግምት ውስጥ በማስገባት ፕሬዝዳንቱ እና የሚመለከተው ወይም አግባብ ባለው ም/ፕሬዝዳንት ለተወዳዳሪዎች (15 ከመቶ) ነጥብ ይሰጣሉ፡፡

I. የአገር አቀፍ የትምህርት ፖሊሲዎችን የማስፈጸም ቁርጠኝነትና አመራርነት (4 ነጥብ)፡

II. የሚመለከተው ዳይሬክቶሬቱ የአገልግሎት ስራዎች ተሳትፎ (4 ነጥብ)፡

III. የግል ተነሳሽነት፣ የተግባቦት ክህሎት፣ መልካም ስምና ሀቀኝነት እና የስትራቴጂካዊ አስተዳደር እውቀት (4 ነጥብ)፡

IV. የዳይሬክቶሬቱን እና የዩኒቨርሲቲውን ዕቅድ የመፈጸምና የማስፈጸም ቁርጠኝነት (3 ነጥብ)፡

## 5.7. ከኃላፊነት መሰናበት

ዲን፣ ምክትል ዲን፣ የትምህርት ክፍል ኃላፊዎች እና ዳይሬክተሮች ባሳዩት ዓመታዊ የሥራ አፈፃፀም ግምገማ መሠረት እንዲሁም የዲስፕሊን ግድፈት ፈጽመው ሲገኙ ሹመት በሰጣቸው አካል ተገምግመው ከኃላፊነታቸው ሊነሱ ይችላሉ፡፡

## 6. አወንታዊ ድጋፍ

(1) በሁሉም የኃላፊነት ቦታዎች ለሴት አመልካቾች ባገኙት የነጥብ ድምር ላይ 5 ነጥብ፣ ለአካል ጉዳተኞች ደግሞ ባገኙት ውጤት ላይ 6 ነጥብ ይጨመራል፡፡

(2) አንድ አመልካች ከአንድ በላይ አወንታዊ ድጋፍ ተጠቃሚ ከሆነ ከፍተኛ ነጥብ የሚያስጠው አንድ አወንታዊ ድጋፍ ማበላለጫ ይያዝለታል፡፡

## 7. ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

(1) በየሥራ መደቡ ቢያንስ 3 ተወዳዳሪዎች ካልቀረቡ ማስታወቂያው ድጋሚ እንዲወጣ ይደረጋል፣ ድጋሚ ከወጣ በኋላ የቀረቡት አመልካቾች ብቻ እንዲወዳደሩ ይደረጋል፡፡

(2) ለሁሉም የኃላፊነት ቦታዎች ማስታወቂያው ለ5 የሥራ ቀናት አየር ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡

(3) ለአካዳሚክ ክፍሎች ዲን፣ ም/ዲን እና የት/ት ክፍል ኃላፊ መወዳደር የሚችሉት ሌክቸረርና ከዛ በላይ የትምህርት ደረጃ ያላቸው አመልካቾች ብቻ ይሆናሉ፡፡

(4) የዩኒቨርሲቲው አመራሮችና ሠራተኞችና የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች አክብረው የመፈፀም ኃላፊነት አለባቸው፡፡

(5) ይህ መመሪያ ወደ ሥራ ሲገባ በሥራ ላይ ያሉ የሥራ ዘመናቸው ያልተጠናቀቀ የመካከለኛና መሠረታዊ አመራሮች የያዙት የኃላፊነት የሥራ ዘመን እስኪጠናቀቅ ድረስ የሚቀጥሉ ይሆናል፡፡

(6) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) እንደተጠበቀ ሆኖ በሥራ ላይ የነበሩ አመራሮች ቦታዎች በሌላ እስኪተኩ ድረስ በማገልገል ይቆያሉ፡፡

(7) በዚህ መመሪያ አሰራር መሰረት በትምህርት ክፍል፣ በአካዳሚክ ዩኒት ዲንና ም/ዲን ኃላፊዎች፣ እንዲሁም በዳይሬክተር የሥራ መደብ ምርጫ ሂደት ላይ ከሠራተኞች የሚቀርቡ ቅሬታና አቤቱታዎችን የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ተቀብሎ ያስተናግዳል፡፡

(8) የአካዳሚክ ዩኒት ዲን፣ ም/ዲንና ዳይሬክተሮች የኃላፊነት ቆይታ ዘመን ሶስት ዓመት ሲሆን የትምህርት ክፍል ኃላፊዎች ወይም በነዚህ ደረጃ ያሉ የስራ ክፍል ኃላፊ የኃላፊነት ጊዜ ሁለት ዓመት ብቻ ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን በሁሉም ደረጃ ያሉ ኃላፊዎች በድጋሚ ለአንድ ጊዜ ብቻ መወዳደር ይችላሉ፡፡

## 8. መመሪው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ የዩኒቨርሲቲው ሴኔት ካጸደቀበት ከ-----/2011 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡